የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ማህበር በደቡብ አፍሪካ
**Ethiopian Community Association in South Africa**
Tel 27824819541, P. O. Box 2834, Johannesburg 2000
e-mail twoubet@yahoo.com, akbafana@yahoo.com,ecsa2020@gmail.com



# ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ያወረሱን አኩሪ የኢትዮጵያዊነት በልደት ቀናቸው ዋዜማ ሲታወስ

ዳኛው ምኒልክ፤ እምዬ ምኒልክ፤ ሲነግሡ ስማቸዉን ያልቀየሩ፤ በልጀነታቸዉ አቤቶ ምኒልክ፤ የአጼ ቴዎድሮስ ደጃች ምኒልክ፤ የራሳቸው እንዲህም የአጼ ዮኃንስ ንጉሥ ምኒልክ፤ በኋላም (1881-1906) ሞዓ አንበሳ፤ ዘእምነገደ ይሁዳ፤ ንጉሠነገሥት ዘ ኢትዮጵያ አጼ ዳግማዊ ምኒልክ ተብለውዋል።

1836 ዓ ም በነኃሴ 12 ቀን፤ በአንጎላላ ኪዳነ ምህረት ምኒልክ ተወልዱ፡: ስማቸዉን የሰጧቸዉ አይታቸዉ የሸዋዉ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ነበሩ። አባታቸዉ አቤቶ በሻህ ዉረድ (በኋላ ንጉሥ ኃይለ መለኮት) ሲሆኑ እንታቸዉ ወይዘሮ እጅጋየሁ ነበሩ። ወይዘሮ እጅጋየሁ ልጃቸዉን ይዘዉ መንዝ ዉስጥ ጠምቄ ከሚባል ገዳም 7 ዓመት ተቀመጡ (1)። ከዚያም በሰሜን ሸዋ እየዞሩ ምኒልክ ከተለያዮ ኦሮሞዎች፤ ከእነ ጎበና ዳጬ ጋር የልጅነት ጓደኝነት አትርፈዋል (1)። ጥያቄዉ፤ ለምን አባታቸዉና አያታቸዉ ከሚኖሩበት አንኮበር እኮረብታ ላይ ከተሠራዉ የ“ላይ ቤት” ዉስጥ አልተቀመጡም ነዉ። የምኒልክን ምነነትንና ማንነትን የሚገልጸዉን ባህሪያቸዉን ካነጸዉ መካከል አንዱ የልጅነት አስተዳደጋቸዉ ነበር።

ዳግማዊ ምኒልክ፤ በአድዋ ላይ በአንድ ቀን ጦርነት በ 1887 ዓም የካቲት 23 ቀን፤ የጣሊያንን ወታደር በማወደማቸዉ ኢትዮጵያ በታሪክ ፊት ነጻ አገር መሆኗን መመዝገብ ብቻ ሳይሆን፤ ለጥቁር ልጅ ሁሉ ኩራትን ስጥተዋል። በአንጻሩ፤ የአድዋን ድል ለማከሸፍ እስካአሁን ድረስ አንዳንድ የነጭ ግላሰቦች፤ ድርጅቶችና አንድንድ ህሊና-ቢስ ተከታይ ኢትዮጵያዊ ታዛጆቻቸዉ የምኒልክን ስም ያጠፋል። በተጨማሪ፤ ባሪያ በመሸጥ ምኒልክ ሀብታም ሆነዉ ነበር እያሉ ስም-አጥፊዎች ያሟቸዋል። ታዲያ፤ “አባይን ያላየ ምንች ያመሰግናል” እንደሚባለዉ፤ እናታቸዉ ወይዘሮ እጅጋዩ በአገልጋይነት ይሠሩ እንድነብር፤ የእጅጋየሁ አባት ደግም ባሪይ እንደንበሩ ተጹፏል (1)። እንዲሁም፤ በዘመኑ “ባሪያ ማለት፤ በገንዘብ የሚሸጥ ብቻ ሰይሆን በጦርነት የሚማረክ ሁሉ፤ ባሪአ ይባላል” ተብሎ ተዘግቧል (1)። መገንዘብ ያለብን፤ በኢትዮጵያ ባሪያ ማለት በእንግሊዝኛ “ስሌቭ” ከሚለዉ የተልየ መሆኑን ነዉ። በቤተመንግሥት ወይም በሀብታም ሰዎች ብቻ ሳይሆን በቤተክህንት ጭምር አገልጋዮች፤ ባሮች፤ ነበሩበት። ከአጼ ምኒልክ ትውልደ-ታሪክ እንድምንረዳዉ፤ ኢትዮጵያዊ ግለሰብ በተፈልገዉ ዓይነት ቢሰየምም ይዋለዳል፡፤ ማእርግም እንድ ግል ችሎታዉ ያገኛል። ሆኖም ይህንን የባሪያ ጉዳይ በመቃወም፤ በተደጋጋሚ ከልብ የመነጨ አዋጅ ምኒልክ አዉጥተዋል። ለዚህም ማሰረጃ አንዱ የሚንልክን ደብዳቤ ብንጠቅስ ለጂማ አባጂፋር በ 1902 ዓም የካቲት 8 ቀን የጻፉት ምስክር ነዉ።

Tel 27824819541, P. O. Box 2834, Johannesburg 2000
e-mail twoubet@yahoo.com, akbafana@yahoo.com,ecsa2020@gmail.com

“..አነተንም ልበድልህ፤ ልጅህንም አምጣና እንደከብት ልሽጠዉ፤ ልለዉጠዉ አትበል። ይህንን ያህል ዘመን አባቶቻቸዉ ካባቶቸህ፤ ልጆቹ ካንተ ጋር አብረዉ ኑረዉ ባሪያ ሊባሉ አይገባም። ባደባባይም ባሪያ ነዉ ብለህ አትሚገት። የሰዉ ባሪያ የለዉም። ሁላችንም የእግዚአብሄር ባሪዎች ነን።...” (1)

በእርግጥ ባርነትን ዛሬ ሁላችንም እንቃውማልን። ግን በዚህ ድርጊት ጥቅም እተገኘበት ድረስ ሥነሥረአቱን ማዉደም ያዳግታል። ለዚህ ነዉ በአሁኑ ጊዜ፤ በያአለበት፤ በአሜሪካ ጭምር፤ አንዳንድ ሴቶች ለዝሙት የሚሸጡት። አሁንም ቢሆን፤ ምንም እንኳ ችግሩን ለመወጣት ቢያቅተንም መቃወማችንን ማቆም የለብንም።

ምኒልክ የአድዋን ጦረነት ሲዋጉ ብዙ ዝግጀት አድረገዉ ነበር። በየመንገዱ ጦሩ በሚሄድበት ሥፍራ ሰራዊቱ የሚመገበዉን አዘጋጅተዉ ነበር። የነበራቸዉ ከፈርንሳይ የገዙት መድፍ፤ ጣሊያን ከነበረ መድፍ አርቆ ይመታል (2)። ከሁልም እጅግ የሚአስደንቀዉ ከታችኘዉ፤ ከመሃል፤ ካላይኛዉ አገር፤ ወገን ሳይለይ፤ በጠቅላላ ጀግና ኢትዮጵያዊ ታዝዞ፤ እንደታዘዘዉም “ጠባዩን በጉያዉ፤ ስንኩን በአህያዉ ይዞ” ለሀገሩ፤ ለወገኑና ለክብር ሕይወቱን ለምሰዋት፤ የኢትዮጵያ መኳንነትና ሠራዊት እንዳለ ዘመተ። ድልን ተጎናጸፈ። ሕዝቡ መሪ ነበረዉ። እምዬ ምኒልክ መሪ ነበሩ።

የምኒልክ ታሪክ ብዙ ነዉ። በ 1848 ዓም ህዳር 1 ቀን፤ አባታቸዉ ንጉሥ ኃይልመልኮት ሞቱ። በህዳር 10፤ ሸዋን ከግዛታቸዉ ሊቀላቅሉ የመጡት አጼ ቴዎድሮስ ምኒልክን ወደ ጎንደር ከዚያም ወደ መቅደላ ወስደው ልጃቸዉን አልታሸን ዳሩላቸዉ፤ እንደልጃቸዉም አዩአቸዉ። በ 1857 ዓም ሰኔ 24 ቀን ሚስታቸዉን ትተዉ ደጃች ምኒልክ ከመቅደላ አመለጡ። ከዚያ በኋላ በሸዋ ሲነግሡ፡፤ ከዚያም ወሎን ሲጭምሩ፤ በኋላ የታቹን አገር ሲያጠቃልሉ፤ 3 ጊዜ አጼ ምኒሊክ የንጉሥነት ዘውድ ደፉ (2፤ 3)፡፡ 2

1. ነኅሴ 24 ቀን 1857 ዓም፤ በአጼ ቴዎድሮስ ዘመን መንግሥት፤ አንኮበር ላይ፤ አቤቶ በዛበህን በጋዲሎ (ግድም) ካሸነፉ ከ 7 ቀን በኋላ።
2. መጋቢት 18 ቀን 1870 ዓም ፤ አጼ ዮኃንስ ለምንሊክ ወሎ ላይ ዘውድ ደፉላቸዉ። ከዚያም፤ በቦሩ ሜዳ፤ በአጼ ዮሃነስ የበላይነት ስለክርስትና እምነት ዉይይት አደምጡ;፡
3. ጥቅምት 4፤ 1871 ደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተክርስትያን ላይ ዘዉድ ደፉ። ከአራት ዓመት በኋል በ 1875 ዓም ጥቅምት 13 ቀን የአጼ ዮኃንስ ልጅ ራስ አራያና የምኒሊክ ልጅ ዘዉዲቱ ተጋቡ። ዘዉዲቱ የ6 አመት ልጅ ነበሩ፡።

የአራተኛዉ ዮኀንስ ግዛት ከ 1864-1881 ነበር፡፡ በዚያዉ ዘመን ንጉሥ ምኒልክ ተበታትነው የነበሩ አካባቢዎችን ወደ ማዕከላዊ አስተዳደር እንዲቀላቀሉ አደረጉ በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኘዉን አገር ፤ እሳቸዉ ባሉበት ወይም በራስ በሚመራ ጦር እየላኩ ወደ ኢትዮጵይ እንዲቀላቀል አደረጉ። የታች አገሩን ማሰባሰብ ብቻ ሳይሆን ደረቡሽ (ሱዳን) ጎንደረን ሲያጠቃ የጎጃሙ ንጉሥ ተከለሃይማኖት ስላልቻሉት፤ በአጼ ዮኃንስ ታዘዉ ንጉሥ ምኒልቅ ወደ ጎንደር ዘምትዋል። ንጉሥ ምኒልክ ሠራዊታቸዉን አዘዞ ሲያሰልፉ የደርቡሽ ቃፊሮች አይተዉ፤ ከመተማ ወዲህ እንደማይመጡ ከምኒልክ ጋር ደርቡሾች ተዋዋሉ (2)።

**የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ማህበር በደቡብ አፍሪካ**

**Ethiopian Community Association in South Africa**

Tel 27824819541, P. O. Box 2834, Johannesburg 2000

e-mail twoubet@yahoo.com, akbafana@yahoo.com,ecsa2020@gmail.com

ይህንንም ዜና ለአጼ ዮኅንስ ነግረዋቸዋል። በኋላ ግን አጼ ዮኅንስ ራሳቸዉ ወደ መተማ ዘምተዉ፤ በጦርነት ቢያሸንፉም እሳቸዉ በ 1881 መጋቢት 1 ቀን አረፉ (2)።

ከ 1881-1906 የዳግማዊ አጼ ምኒልክ ንጉሥነገሥት ዘመን ነበር። በ 1882፤ ጥቅምት 25 ቀን አጼ ምኒልክ የንጉሠነገሥት ዘውድ ደፉ። በዘምናቸው ጠላትን ድል ነሱ፡፡ በዓለም ኢትዮጵያ ነጻ አገር መሆኗን አሳወቁ፡፡ አስመሰከሩ። ኢትዮጵያም የመሀከል ግዛት እንዲኖሩት አደረጉ። በአገሪቷ ትምህርት ቤት፤ ስልክ፤ፖስት፤ ኢሌክትሪክ፤አቶሞቢል፤ባህርዛፍ፤ ሆስፒታል፤ ባንክ፤ ገንዘብ፤ ማተሚያ፤ ጋዜታ፤የጽህፈት መኪና፤ (1) ወዘተ፤ ከፈቱ ወይም ከውጭ አስመቱ። በ1871 ዓም ጥቅምት 17 ቀን ያስቆረቆሯትን አዲስ አበባ ከተማን በባብሩ ከጂቡቲ እንድትገናኝ ለመጀምሪያ በ1887 ዓም (1894-ኡሮጳዊ) ተዋዋሉ። አማካሪያቸዉ ወዳቸው የሆነዉ የስዊድን ተወላጅ፤ ኢልግ፤ የባቡር ሃዲድ "ሼር" ኢንዲኖራቸዉ ሲጠይቃቸዉ፤ የባብሩ ሀዲድ የሚሂድበትን ቦታ ለ 99 ዓመት አዋሱት። በ1889 በድጋሚ ስለባቡር ዉል አደረጉ።

በ1895 ዓም (1902 እንደ አውሮጳ አቆጣጥር) በእንግሊዝ መልክተኛ አማካኝነት በኢትዮጵያና በእንግልዝ መካከል ዉል ሲያደረግ አባሪ በተጻፈ ስምምነት መሠረት 1000 ጊኒ ከአባይ ከሚወስደዉ የዉሀ ጥቅም በየአመቱ የአንግሎ ሱዳን አስተዳደር ለኢትዮጵያ እንደሰጥ መዋዋሉን አጼ ኃይለሥላሴ በጻፉት መጽሕፍ ገልጸዋል (4)። ቢሆንም፤ በዋናዉ ዉል የእንግልዝኛዉ ጽሑፍና የአማርኛዉ የተለያዩ ሁኔታዎችን ያሳያል፡፡ ያለ እንግሊዝ ፈቃድ በአባይ ወንዞች ግደብ ("ዳም") እንዳይሠራ በአንቀስ 3 በእንግሊዝኛ ሲገልጽ፤ በአማርኛው ደግም "ከእንግልዝ መንግሥት ጋር አስቀድም ሳይስማሙ ወንዝ ተዳር እዳር የሚደፍን ሥራ ለመሥራት ለማንም ፈቃድ እንዳይሰጡ በዚህ ዉል አደርገውል" (5) ይላል። ታዲያ፤ የወንዝ ግድብ ኢትዮጵያ ብትሠራ ወይም በከፊል ወንዞችን ወደ ሌል ቦታ፤ ለምስኖ ወይም ለሌላ ጥቅም ኢትዮጵያ ብታዉል፤ በወንዙ ውሀ እፈሰሰ ድረስ ዉሉ አይከለክልም (6)። አጼ ኃይለሥላሤ እንግልዝን በ 1916 ዓም በጎበኙ ጊዜ ግድብ ለምሥራት የፈልጉትን መሀንዲስ እንድሚኮናተሩ ለእንግልዝ ጠቅላይ ሚንስቴር ነግረዉት ነበር። እሱም የአሚሪካን እንጂሮችና መሀንዲሶች ጥሩ መሆናቸዉን ገልጾ ነበር (4)። በተጨማሪ፤ ዋናዉ ውል፤ በአንቀጽ 4 በእንግልዚኛዉ ጽሑፍ ሱዳን ባእንግሎ ግብጻዉ መንግሥት ስር ነው የሚለዉ፤ በአማርኛ በተጻፈዉ ውል "የእንግሊዝ መንግሥት ሱዳንን እለቀቀ ድረስ.." ብሎታል (5)። በማያወላዉል ሁኒታ ዉሉ የሚጸናዉ አጼ ምኒልክ በሚግባቸዉ በአማርኛ ቋንቋ ነዉ። እንግሊዝ ከቅኝ ግዛቷ ስትላቅ ዉሉ አብሮ ያልቃል ብለው ዳግማዊ ምኒልክ ተሰማምተዋል። ይህ ዓይነቱ ስሌት በቅኝ ግዛት ከመጡ ጎርቤቶቻቸዉ ጋር ውል ሲያደርጉ ምኒሊክ የሚከተሉት መላ ነበር። ባንቀጽ 17 የዉጫሌ ዉል ባማርኛና በአዉሮፓ ቋንቋ የተለያዩ ትርጉሞች በመስጠታቸዉ ምክንያት የአድዋ ጦረነት መጣ። ከአድዋ ድል በኋላ አዲስ አባብ በ1899፤ ጥቅምት 17 ቀን፤ በጣሊያንና በኢትዮጵያ በተደረገዉ ዉል፤ በውጫሌ የተረገዉን ስምምነት በሙል ይሰርዛል። ይህ እንዳል ሆኖ፤ ዉሎቹን ሁሉ ጥሶ ፋሺስት ጣሊያን ድፍን ኢትዮጵያን በ 1928 ሲወርር ዉሎቹን ሁል አፍረሷል። በጣሊያንና በኢትዮጵያ የተደረገዉ የቀድም ዉሎች ሁሉ ፈርሰዋል። ሆኖም፤ እጅግ የሚያሳዝነዉ ወያኔ-ትግሬና ሻአቢያ፤ በጉልበት የኢትዮጵያ ገዢ ነን ካሉ ጊዜ ጀምሮ በፈረሱ ዉሎች ተነስተዉ፤ እነኛንም ዉሎች አጓጉል ተርጉመዉ፤ ኢትዮጵያን አዋረድዋታል። ላልፉት 40 አመታት ገደማ ደርግ፤ ወያኔ-ትግሬና ሻአቢያ የኢትዮጵያን እድገት ቢቁራኟትም፤ በዚህም መክንያት ዓለም መጥቆ ሲሄድ የኢትይጲያን እድገት ወደኋላ ቢጎትቱም፤ የምኒልክን የትዉልድ ቀን ስናከብር ስለወዳቂ ጠባይ በማዉሳት ልናዝን አይገባም። 3

የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ማህበር በደቡብ አፍሪካ
**Ethiopian Community Association in South Africa**
Tel 27824819541, P. O. Box 2834, Johannesburg 2000
e-mail twoubet@yahoo.com, akbafana@yahoo.com,ecsa2020@gmail.com

አጼ ምኒሊክ ኢትዮጵ ኢትዮጵያዊነትን ከአፍሪካዊነት ለይተው ያላዩ የአውሮፓያውያንን አፍሪካን የመቀራመት አጥበቀው የተቃወሙና የታገሉ፤ለጥቁር ህዝብ የነፃነት ትግል አርማ ፈርቀዳጅ በመሆናቸው እንዲሁም ለኑኩሩማን፤ጆሞ ኬኒያታ፤ ኔልሰን ማነዴላ እና ሌሎችም ሁሉ ለአፍረካ ህዝቦች የነፃነት ትግል መሰረት በመሆናቸው አፍሪካውያን ሁሉ እናከበራቸዋለን ታሪካቸውንም እንዘክራለን።

አጼ ምኒልክ፤ ለበርካታ-ትወልዳቸዉ ትምህርት የሰጡ፤ ልበ-ሙል ጀግና፤ በዳኝነታቸዉ የታወቁ፤ ከአዉሮፐ የመጣ ወታደር ደምስሰዉ የአገራቸዉን ነጻነት ያስከበሩ፤ በዚህም ድርጊታቸዉ ነጻነት ፈላጊ ሁል ያደንቃቸዉ፤ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ንጉሠነግሥት ስለነበሩ እንኳን የትውልድ ቀናቸዉን ላማውስት አበቃዎ እንላልን፡፡

“እኛም ጥቁር እናንተም (ደርቡሽ ሱዳኖች) ጥቁር እንተባበርና የ ብሪታኒአን የንጉስ አገዛዝ እንዋአ”
Raymond Jonas, Adwa Victory: A Definitive African Victory over Empire, Harvard University Press,2011

“ኢትዮጵያ ከእግዚአብሔር በቀር የምትፈራው የለም እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ትዘረጋለች ጠንካራ ያላችሁ በጉልበታችሁ የደከማችሁ በፀሎታችሁ ተከተሉኝ”

“አፍሪካን አውሮፓውያኑ ሲቀራመትዋት ዝም ብዩ አላይም እታገላለሁ”

ለቤንቶ ሲልቫኒ እንዲህ አሉት “ የጥቁር ህዝብ ነፃ አንዲወጣ የምታደርገውን ትግል እና ሐሳብ አደንቃለሁ እደግፋለሁ”

## ዋቢ መጽሀፍትን መጣጥፍ

1. ፓዉሎስ ኞኞ አጤ ምኒልክ
2. ተክለ ጻዲቅ መኩርያ ዐጼ ምኒልክ
3. ጌታቸው ኃይሌ ባሕረ ሐሳብ
4. ቀዳማዊ ኃለሥላሤ ህይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ
5. Edward Ullendorf, The Anglo-Ethiopia Treaty of 1902, Bullet School of Oriental . and African Studies.
6. ሀብተ ጊዮርጊስ ቸረነት Replacing language –based-group ጵolitics of the EPLF/TPLF

==